# አገርና ሕዝብን ለምዳን መተባበር ቀጠሮ የማይሰጠው ተግባር ነው!!

January 12 /1/16

ጃንዋሪ **12 2016** ዓም በእሳት የሰማነው ሰበር ዜና በጣም የሚያስደነግጥ ግን ሊሆን የሚችል እውን ተግባር ነው። የሕዝብ ትግል በገፋ እና አንባገነንን መንግስት ስጋት ላይ እየጣለው ሲሄድ መቸውንም በታሪክ እንዳየነው እንደነዚህ አይነት መንግስታት ሀላፊነት አይሰማቸውም እና በእጃቸው ያለን ማነኛውንም የጥቃት በትር ከመወርወር አይመለሱም።

ከርዋንዳ ምን እንማራለን**?**

ከ **1973** እ ኤ አ ጀምሮ የርዋንዳን በትረ መንግስት ይዞ የዘለቀው አንባገነን ጀኔራል **(General Juvenal Habyarimana)** እራሱ ያወጣውን ህገመንግስ ሁለት ግዜ ቀይሮ አራት ተከታታይ ምርጫወችን ያለተወዳዳሪ ከወሰደ በህዋላ በአምስተኛም የርዋንዳ ፓትርዮቲክ ግንባር በተባለ ድርጅት ችግር ላይ ሲወድቅ እንደ አማራጭ ስልጣን ማካፈል ሲሆን ይህ ስምምነት በአንባገነኑ ጀኔራል እና በግንባሩ ሲደረግ የቱትሲ አክራሪወች እጅግ በመበሳጨት የዘር ጥላቻን ማራገብ ይጀምራሉ። የነዚህ ጽንፈኞች እድል ሞልቶ በድንገት የብሩንዲን እና የርዋንዳን ሁቱ መሪወች የያዘች አውሮፕላን በታጋዮች ተመታ መውደቅ እና ባለስልጣናቱ በአደጋው መሞት የጀኖሳይዱ ጅማሮ ምክንያት ለመሆን በቅቷል። የዘር ጥላቻ ለአመታት የተዘመረባት እርዋንዳም ሆነች ብሩንዲ የህዝብ እጣ ፈንታ መተላለቅ ሆኖ **800000** የቱትሲ ዜጎች ህይወት በአጭር ቀንና በሰአታት ተቀስፏል። ለዚህ ታሪካዊ የአለማችን የ **20** የመጨረሻ አመታት ተወቃሽ እና የችግሩ ጀመሪ ማንም ይሁን ማን ታሪክ ግን ጥቁር ቀለም ቀብታው አልፋለች። እንደሚታወቀው ከዚህ ፍጅት በፊት ይህችው አገር በመካከለኛው አፍሪካ የህዝብ ብዛት እና ወሊድን አለመቆጣጠር በሚል በአውሮፓውያን ስትወቀስ ቆይታ መዝጊያው ሕዝብን ከሕዝ ያጫረሰ ክፉ ነገር መከሰት ሆኗል።

እንደሚታወቀውና ብዙ የአገራችን ምሁራን እና ለህዝብ አሳቢ አገርወዳድ ዜጎች ደጋግመው ቢናገሩም ስሚ አጥተው የዛሬ **25** አመት ወታደራዊ መንግስት እራሱ በፈጠራቸው ቅራኔወች ተተብትቦ በህዝብ አክ እንትፍ ተብሎ ሲተፋ እድሉ የገጠማቸው እነዚህ አሁን በስልጣን ላይ ያሉት ኢትዮጵያንና ሕዝቧን አምርረው የሚጠሉ ሀይሎች በመሆናቸው አገሪቱን የባህር በር አሳጥቶ ከማዳከም ጀምሮ የውጭ ጠላት ሊሰራው የሚከብድ ብዙ ዘረኛ የሆነ እርስ በእርስ የሚያባላ ተግባራትን ፈጽመዋል። የብዙ ሽህ አመታት ውጤት የሆነው በባህሉ ከማንኛው ዛሬ በሀብት ከበለጸጉት ሁሉ የላቀው ኩሩ ሕዝብ ነገረ ስራቸውን አይቶና ተጠይፎ ተቻችሎ ያሰቡትን ሳይተገብር እስከ ዛሬ ቆይቷል። ከዚህም በኋላ ይቀጥላል። ይህ ሲባል ክፉ ተግባራትን ልክ በአርባ ጉጉ፣ በበደኖ፣ ብሎም በጎጃም መተከል በወልቃይት ሰሞኑን ደግሞ አንድ ሕዝብን ለሁለት ለያይቶ ለማባላት የከጀሉት ሁሉ አይነት ደግመው አይሞክሩትም ማለት አይደለም። በዛሬ ሰበር ዜናወች የሰማነው ለጀሮ ከባድ የሆነን ክፉ ስራ ለማክሸፍም ሆነ የዚህ በመካሄድ ላይ ላለ ንቅናቄ ውጤታማ እንዲሆን ሦስት መሰረታዊ ተግባራት መከወን ይኖርባቸዋል።

**1-** የድህረገጽ ሚዲያወች፤ በየከተሞች የሚሰራጩ ራዲዮ ጣቢያወች፤ እና ቴሌቪዥን ዜናወች በሰሜን የአገራችን ክፍል ለድንበራችን ዘብ ሆኖ መስዋእት የሚሆነውን። በወልቃይት ጸገዴ የዘር ማጥፋት የአገርና ሕዝብ አድን ጥሪ በማድረግ ላይ ያለውን ከደቡባዊ ሕዝባችን እንቅስቃሴ ጋር ቀን በቀን መዘገብ ሕዝብን በአንድ መነሳቱን ያሳያል፤ ደግሞም የህዝብ ስሜትን ያጠናክራል።

**2-** በድርጅት የተሰባሰቡ የፖለቲካ፣ ሰብአዊ መት እና ሞያዊ የሆኑ ሁሉ በአንድ ጃንጥላ እንዲጠቃለሉ፤ ለጋራ አላማ በአንድ መቆም እንዲችሉ መሆን ይኖርባቸዋል። ለዚህም በውስጥ ወይንም በውጭ ብለው አሁንም ጠላት ይቆጣናል ወይንም ይጨርሰናል ብሎ ነገርን ማቆም እና ልክ እንደቅንጅት እና ህብረት **(1997)** እንደሆነው በአንድ መነሳት። በጋራ መስራት ይጠበቃል። ቢያንስ ተመሳሳይ አቋም ያላቸው ወደአንድ እንዲመጡ ይጠበቃል። በተለይም በግለሰቦችና በውስጥ ቅራኔወች የተለያዩ የአንድ ድርጅት አባላት ይህን የትብብር በጎ ነገር አራያ በመሆን ማስተባበር ይጠበቃል።

**3-** በተለይ የኢትዮጵያን ሕዝብ ስም የያዙ ሚዲያወች ፋይዳ ቢስ ጥቃቅን ተቃርኖን ወደጎን አድርገው የህዝባችንን ስቃይ፣ ትግል፣ ሞትና መንገላታት በሁሉም አካባቢ የሚሆኑትን ለህዝብ አይንና ጆሮ ሊያደርሱ ሀላፊነትም ግዴታም ነው። በተለይ ዛሬ እንዳየነው። ብዙ አዋቂ ዜጎች ቀደም ብለውም ሲያስጠነቅቁን እንደነበር ወያኔ የመጨረሻ ጠርዝ ላይ ስትደርስ ሕዝብን የማጋጨቱ ካርታ ዋነኛና የመጨረሻው መጀመሪያ እንደምታደርገው ይገመታል እናም ይህ ደግሞ በህዝባችን፣ በንቅናቄውም ጉዳት እንዳያስከትል በሰፊው መዘገብ። ሕዝብን ማስተማር። ማሳወቅ ይጠበቃል።

ከአንድ ወር በላይ በመካሄድ ላይ ያለው ሕዝባዊ አመጽ በማንም ተጽእኖ የተነሳ ሳይሆን በመሬት ላይ የሚታየው የግፍ እና በደል ጽዋ ሞልቶ በመፍሰሱ ነው። ይህ ህዝባዊ አመጽ አንድ ገጽና መልክ ባይኖረውም ከሰሜን እስከ ደቡብ፤ ከምስራቅ እስከ ምእራብ ተቀጣጥሏል። የሚቆም አይሆንም። ወያኔ የ **1997** ን የህብና የአገር ተገቢ ጥያቄወች ደፍጥቶና ህዝብን ገሎ ዳግም ሕዝባዊ መነሳሳት እንዳይኖር ማሳረጊያ የሰጠ መስሎት ነበር። ሆኖም እነዚህ ደናቁርት ያልተገነዘቡት። እስወዲያኛውም አይገባቸውም በደል እስካልቆመ። ጭቆና እስካልተወገደ የህዝብ ጥያቄ ይብስ ከሮና ፍሞ እንደሚመጣ ታሪክ ደጋግሞ የአለምን ህዝብ አስተምሯል።

ይህ በእዚህ እንዳለ ፖለቲካና ፖለቲከኞች ብዙ ጊዜ ሲሰሳቱ ተስተውሏል። የስህተት መነሻውና መዳረሻውም የህዝብን ጥያቄ በቅጡ ማስተናገድ አለመቻል ሲሆን፤ ተጨባጭ ሁኔታን አንብቦ ተገቢ የትግል መስመር አለመከተል ነው። ይህ ደግሞ በአገራችን ደጋግሞ ተስተውሏል። እስኪ ዘርዘር ባለ መልኩ ላቅርብ

የህዝ ትግል ስንል

ዛሬ በሀገራችን የደቡብ፤ መራብ እና ምስራቅ የተቀሰቀሰውን ሕዝባዊ አመጽ የተለያዩ የፖለቲካ፣ ሲቪል እና ወያኔን ጨምሮ ትርጓሜ ለመስጠት ሲከጅሉ ተስተውሏል። ለምሳሌ ወያኔ ይህን የህብ ጥያቄ በሦስት መልክ ለማክሸፍ እየተሯሯጠ መሆኑን በለፉት ሳምንታት አይተናል። በዋነኝነት እና ለአመታት የተጠቀመበት ሕዝብን በዘር፣ በቋንቋ፣ በጎጥ መለያየት ሲሆን በተለይም ህዝባዊ ቁጣ በተነሳበት በዚህ ሰሞን ይኸውን ታክቲክ ሞክሮት ከሽፎበታል። ለመክሸፉ ደግሞ እስኪ እንደሚከተለው እንመልከት። ወያኔ ይህችን ሰፊ ሀገርና ሰፊውን ህዝባችንን ለ **24** አመታት እርሱ ገድሎ ህዝብ እንደገደለ በማስመሰል ሲያጋጭ አይተናል። ለዚህ በተለያዩ የደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ ክልሎች አይተንል። ለምሳሌ ከጉራ ፈርዳ፣ ከበደኖ አርባ ጉጉ፤ ብሎም በቅርቡ ደግሞ ከቻግኒ መተከል ከኖሩበት ተፈናቅለው እርሱ የፈጠረውን እርሱ ገላይ እንዲሆን ብሎም ሕዝብ በሕዝብ ቂምና ቁርሾ እንዲይዝ ለማድረግ ቢሞክርም የበደሉ ገፈት ቀማሽ ግን የልቡን በልቡ ይዞ መከራውን ተቀብሏል። በጎንደር በአንድ ሕዝብ መሀል ገብቶ ያውም በተዋለደ፤ ለብዙ ሽህ ዘመን አንድ ወንዝ በተጋራ ዘመዳሞች መሀል አሽከር **(**ባንዳ**)** ፈልፍሎ ደም ለማቃባት እንደሞከረ ተስተውሏል። ይህ ሁሉ ጉዳት ቢያስከትልም የማታ ማታ ትርፉ ለወያኔ ዜሮ ይሆናል እየሆነም ነው።

አገሪቱን በቋንቋ ሸንሽኖ እንዲህ የህዝብ ቁጣ ሲነሳ ባለፉት አመታት አንዱን ከሌላው በማባላት ሲያከሽፍ ቢኖርም ዛሬ ግን ግፍ ሞልቶ ሲተርፍ ማጠፊያው ቢያጥርበት ታሪካዊ ሂደት ነውና አያስገርምም። ግን ወያኔ የተባላ ዘዴውን ከመጠቀም ወደኋላ አለማለቱን በሚያካሂደው እርካሽ ፕሮፖጋንዳ እየታዘብን ነው። ለምሳሌ ንቅናቄውን የተወሰነ ቋንቋ። ወይንም የተወሰነ የፖለቲካ ስብስብ በማድረግ በሌሎች ጥርጣሬ እንዲያድር ብሎም ከእርሱ ጎን ለማሰለፍ ሞክሯል፣ እየሞከረም ነው። በቅማንትና በአማራ ብሎ የሞከረው ደፋር ሀላፊነት የጎደለውን ሰይጣናዊ ሙከራ ማስታወስ ያስፈልጋል። ይህን ያልተረዱ የዋህ ፖለቲከኞች ትንሽም ይሁኑ ወይንም ሌላ የወያኔን የዘር እና የክልል ቋንቋ ሲደግሙት እየተስተዋለ ነው። እዚህ ላይ ሰፊው ህዝብ ከሌላው ግዜ በተሻለ ከሰሜን እስከ ደቡብ።

ከምስራቅ እስከ ምእራብ የተቀጣጠለውን እየተቀላቀለው እንጅ እየራቀው አለመሆኑ በጎንደር ጠላት የጫረው እሳት በህዝብ ልጆች ከሽፎ ጥያቄው የመሬትና የድንበር ሆኖ አይኑን አፍጦ መጥቷል።፡በኦሮሚያ ወጣቶች የተነሳው ምንም ይሁን ምን የመሬት ጥያቄ መልኩና አይነቱ ይቀየር እንጅ ከዛሬ አርባ አመት በፊት ሚሊዮኖች ያነገቡት እና የዘመሩለት የመሬት ላራሹ ጥያቄ መሆኑ ከመቸውም በላይ ግልጽነት ይዟል። ዳግም አንባቢ እንዲረዳልኝ የምፈልገው ወያኔ ጸረ ልማት ምንትሴ ሊለው ቢከጅል እና ትቂት ደካሞችን አሳምኖ ሊያሰልፍ ቢሞክር አይገርመኝም። እውነታው ግን የህዝብን መሬት ዘርፎ ከውጭ ለሚመጣ አይስጥ። ዜጎች በአገራቸው ባንድ ጀንበር ቤት የለሽ አይሁኑ። ወይንም ልጅ የሚያሳድጉበት። ከእጅ ወደ አፍ ቢሆንም የእለት ጉርስ እና ልብስ ሽፋኙ ያለች የሌለች ንብረታቸው አይወሰድ ነው።

እናም ይህ ደግሞ ሦስትና አራት ትውልዶችን ያሳለፈ ጥያቄ መልስ ይሻል። ወያኔ ግን መልስ ሊሰጥ አይችልም። ወይንም የወያኔ ሎሌወች እነ አባዱላም ሆኑ ሙክታር የሚመልሱት አይደለም። በሰሜን የቀረበውም ጥያቄ ይኸው ነው። ወያኔ ከጎንደር የወልቃይት ጸገዴን፣ የጸለምትን መሬት አግበስብሶ ለኔ ወደሚለው ክልል ደርቦታል። ይህን በእውሸት የተጨመረ የግፍ ስራ የእኔ የሚለውን ሕዝብ አሳምኖበታል እናም በአንድ ጀንበር ሊመልሰው የሚችል አይደለም። ይህን መሬት ለመጠቅለል በአገራችን ታይቶ የማይታወቅ ወንጀል ፈጽሟል። የአንድ አካባቢን አንድ ተከታታይ ትውልዶች ደግሞም ወንድ ልጆችን መትሯል። እናም ይህ ወንጀል የሚመለስ ሳይሆን ወያኔን በማስወገድ የሚከወን ነው። ይህን ስል ሕዝብ ከሕዝብ ተጣልቶ አያውቅም። ግፈኛው ሲወገድ በአንድ ጀንበር ሰላምና ፍቅር ይተካዋል።

## ምን መደረግ አለበት**?**

**“**ምን ቢቃጠሩ ደረሰ ቀኑ ይላሉ**”** ላለፉት **10** አመታት በተለይም ከምርጫ **1997** ማግስት ጀምሮ በአገራችን ለውጥ ፈላጊወች የተንሰራፋው ተስፋ መቁረጥ እና ግራ መጋባት በሕዝብ አመጽ ተቀስቅሷል። ይህ የህዝብ አመጽ ደግሞ መሪ ይፈልጋል። አጋዥ ይሻል። ከሁሉም በላይ የፈሰሰው ደም ብላሽ እንዳይቀር አጋዥ ያስፈልገዋል። ትብብር አንድነት የምንለው ሀይል ቃል ማለት ነው። ጥያቄው የጋራ ነው። ከላይ እንዳመለከትሁት በሰሜን ለአመታት የቆየ። ሕዝብ ከቀየው ተገፍቶ በአገሩ ባእድ እና ስደተኛ የተደረገበት ሁኔታ ነው የወልቃይትን የሕዝብ ጥያቄ ያፋመው። ይህ ጥያቄ በተደራጀ መልኩ ባይስተጋባም በጎጃም ለአለፉት አምስት አመታት ሕዝብ ወልዶ ከብዶ ከኖረበት ተፈናቅሎ ባገሩ ስደተኛ እደተደረገ በተከታታይ አይተናል። የግፍ ብዛት እንዲሉ በጎዛምን እና ማቻክል ወረዳወች ለአከለ መጠን የደረሱ ልጃገረዶችን በክትባት ስም የተፈጸመው ወንጀል ከምር ጣሊያን በህዝባችን ከሰራው በላይ ከባድ ወንጀል ነው። ዜጎችን ሳያውቁ እና ሳይፈቅዱ በዘር ሀረጋቸው ወይንም በሚናገሩት ቋንቋ ወንጀለኛ ሆነው የማምከን ወንጀል መፈጸም ሁሉ ታይቷል እና ይህ ሕዝብ ከከፋው እና ከተገፋ ቆይቷል። ከዚህስ የባሰ ምን ወንጀል ሊፈጸም ይችላል**?** ስለሆነ እየተካሄደ ያለው ሕዝባዊ አመጽ ስፋት እና ጥልቀት እንዲኖረው መተባበር ያሻል። ይህን ጉግ ማንጉግ የዘረኞች ክምችት በሁሉም ቦታ ማዋከብ የነገ የሚተው አይደለም። ወያኔ ዘረኛም፤ ጠባብም የሆነ የአናሳ ቡድን ነው። ጉልበቱ የህዝብ አለመተባበር። መለያየትና መከፋፈል እንጅ ከነበሩን አንባ ገነኖች ሁሉ ያነሰ

እጅግ ደካማ ድርጅት መሆኑ ሊታወቅ ይገባል።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር **!!!**

መንግስቱ ሙሴ

**http://www.ethiopanorama.com/**